ቁጥር OFAGF-03.6/1/340
ቀን 25/07/2015

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለክብርት ወ/ሮ አለምፀሐይ ጳውሎስ

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ኃላፊና

የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር

ለክቡር ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገ/ሚካኤል

የኢ/ፌ/ፖ/ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል

በርዕሱ የተጠቀሰውን የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 17 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 14 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 31 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አበራ ታደሰ
የፌዴራል ም/ዋና ኦዲተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

የኦዲት ሪፖርት

መጋቢት/2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል። ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሂሳብ ሪፖርቶች፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች(Basic of Audit Opinion)፣

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. **ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ክፍያ፣**

   የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012 ክፍል 2 አንቀጽ 5 የቀን ውሎ አበል ተመንና አከፋፈል በሚለው ስር ተ/ቁ 2 ላይ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታው ውጭ ወደ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ መመለስ ካልቻለ ውሎ አበል እንደሚከፈል ይገልጻል፡፡ ኮሚሽኑ በመመሪያው መሰረት ክፍያ የሚፈፅም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ ሰራተኞቹ በመስሪያ ቤታቸው ውስጥ ቅዳሜና እሁድ ለሰሩበት የቁርስ እና የምሳ የውሎ አበል ክፍያ በሚል በድምሩ ብር 76,143.90 ያለአግባብ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

2. **ከመመሪያ ውጪ ከግለሰብ ኪስ ተከፍሎ የተወራረደ የወጪ ሂሳብ በተመለከተ፣**

   የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለ መንግስት ገንዘብ ክፍያ አንቀጽ 6 መርሆች ንዑስ አንቀጽ 1 የመንግስት መስሪያ ቤቶች በጀት ክፍያ የሚፈፅመው ወይም ወጪ የሚደረገው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ንዑስ አንቀጽ 2 የበጀት ዝውውር ወይም የተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም አይቻልም፣ እና ንዑስ አንቀጽ 3 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ የሚፈፀመው ወይም ወጪ የሚደረገው በጥሬ ገንዘብ፣ በቼክ፣ በሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ በባንክ ዝውውር የክፍያ ማዘዣ በመሙላት ወይም ወደ ባለመብቱ የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ ነው በማለት ይገልጻል፡፡ ኮሚሽኑ በመመሪያው መሰረት ክፍያዎችን እየፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

   በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ:-

   - በቀን 5/5/2014 የባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 266072 የሂሳብ መደብ 6252 እና 6255 ብር 8,699.53 የተለያዩ Forensic DNA Laboratory

Equipment አክሰሰሪ ዕቃዎች ከተለያየ ሀገር በኢትዮጵያ አየር መንገድ በኩል ገቢ የሆነውን የመጋዘን ኪራይና የጉልበት ሰራተኛ ክፍያ እና

- በቀን 6/12/2013 የባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 265182 የሂሳብ መደብ 6233 ብር 27,979.33 የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን አመራሮች በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ዙሪያ ውይይት ሲያደርጉ ስብሰባው ቀኑን ሙሉ ስለነበር እና ከጉዳዩ አፋጣኝነት አንፃር ከግል ኪሳቸው ቁርስ፣ ምሳ እና እራት ገዝተው ያቀረቡ በሚል፤

በድምር ብር 36,678.86 ከኪሳቸው እንዳወጡና እንዲከፈላቸው በጠየቁት መሰረት ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ክፍያው በገንዘብ ያዥ በኩል መከፈል ሲገባው በግለሰቡ እንዲከፈል የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር፣ የኮሚሽኑ አመራሮች ስብሰባ ላይ መሆናቸውን እና የተሳታፊዎችን ብዛት የሚገልጽ ማስረጃ ሳይቀርብ ከመመሪያ ውጭ ከግል ኪሳቸው ክፍያ የተፈፀመና በመወራረዱ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪዉ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪዉን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪዉ በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያው ይገልፃል፡፡ በዚህም መሠረት የዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚፈፀሙ ክፍያዎች መመሪያውን የተከተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጀስቲክ ዋና መምሪያ በቀን 29/11/2013 የባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 265140 የሂሳብ መደብ 6271 ብር 1,754,427.04 ከመከላከያ ፋውንዴሽን አዳማ ጋርመንት ኢንዱስትሪ በ2013 በጀት ዓመት ለ20ኛ ዙር ሰልጣኞች እና አሰልጣኞች አገልግሎት የሚውል የቱታ እና የወይራ ኮፍያ ለተፈጸመ ግዥ በበጀት ዓመቱ ክፍያ መፈፀም ሲገባው ሳይከፈልና በተከፋይ ሂሳብ ሳይመዘገብ ከበጀት ዓመት ውጭ በ2014 በጀት ዓመት ክፍያ በመፈፀም የተመዘገበ መሆኑ፣

- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የጤና አገልግሎት ዋና መምሪያ በድምሩ ብር 7,922,577.13 በ2013 በጀት ዓመት ተገዝቶ አገልግሎት የዋለ የመድሀኒት፣ የህክምና መርጃ መሳሪዎች እና የምግብ ዕቃዎች ግዥ በበጀት ዓመቱ ክፍያ መፈፀም ሲገባው ሳይከፈልና በተከፋይ ሂሳብ ሳይመዘገብ ከበጀት ዓመት ዉጪ በ2014 በጀት ዓመት ክፍያ በመፈፀም የተመዘገበ መሆኑ፣

በአጠቃላይ ድምር ብር 9,677,004.17 በበጀት ዓመቱ ክፍያ መፈፀም ሲገባው ሳይከፈልና በተከፋይ ሂሳብ ሳይመዘገብ ከበጀት ዓመት ዉጪ በ2014 በጀት ዓመት ክፍያ በመፈፀም የተመዘገበ በመሆኑ የ2014 በጀት ዓመት የወጪ ሂሳብን ያለአግባብ ከፍ እንዲል ያደረገው መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>በሞዴል 19 ገቢ ቢሆንም በንብረት ክፍል ያልተገኘ ወርቅ በተመለከተ፣</u>

በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ 9/2003 በክፍል አምስት ተራ ቁጥር 8 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ 5/2003 መሰረት የጠፋ ንብረትን በተመለከተ ከመዝገብ እንዲሰረዝ ካልተደረገ በስተቀር በኃላፊነት ሥር የነበረ ንብረት ሲጠፋ በገበያ ዋጋ መሰረት ተሰልቶ መከፈል ወይም ንብረቱን መተካት እንዳለበት ይገልፃል፡፡

ይሁን እንጂ በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በቀን 13/09/2014 በሞዴል 19 ቁጥር 12942 የፌ/ፖ/ንብ/አስ/ ዋና ክፍል ለፌዴራል ፖሊስ አመራር እና አባል ለሽልማት ተብሎ ከሎጅስቲክ መምሪያ በቀን 27/10/2014 በቁጥር ገበ103/22/47 ለወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ በሞዴል 20 ቁጥር 0887779 አንድ መቶ ሶስት (103) ግራም በብር 18,180,684.16 የተገዛውን ወርቅ ወጪ ሆኖ የተረከበ ቢሆንም ወርቁ በንብረት ክፍል ውስጥ ያልተገኘ እና ለታለመለት አገልግሎት ያልዋለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የኮሚሽኑን የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም የተመለከተው የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአግባቡ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)፣

1. **የቀን ውሎ አበል ቅፆችን በአግባቡ ሳይሞሉ የተፈፀመ ክፍያ፣**

   የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012 ክፍል 3 አንቀጽ 9 ለቀን ውሎ አበል ክፍያ የሚሞሉ ቅፆች ተ/ቁ 1 ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታ ውጭ ወደ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ከመላኩ በፊት የቀን ውሎ አበል መጠየቂያ፣ መክፈያና መፍቀጃ ቅፆች ለጉዳዩ አግባብ ባለው ሰራተኛ ወይም የስራ ኃላፊ እንዲሞላ ይደረጋል። በተጨማሪም ተራ ቁጥር 2 የቀን ውሎ አበል እንዲከፈል የጠየቀ የስራ ኃላፊ በሰራተኛው የተሞላ ቅፅ በትክክል መሞላቱን ያረጋግጣል ይላል። ኮሚሽኑ በመመሪያው መሰረት ክፍያዎችን የሚፈጽም መሆኑን ለማረጋገጥ የውሎ አበልና ጥቅማጥቅም ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፣

   - በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጀስቲክ ዋና መምሪያ በድምሩ ብር 169,601.70 የውሎ አበል የተከፈላቸው ሰራተኞች በሚሄዱበት ወቅት የውሎ አበል መጠየቅያ፣ መክፈያና መፍቀጃ ቅፆች ሳያስሞሉ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣
   - በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ በድምሩ ብር 2,840,973.10 የቀን ውሎ አበል መጠየቂያ፣ መፍቀጃና መክፈያ ቅፆች በአግባቡ ሳይሞሉ ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ፣

   በአጠቃላይ ድምር ብር 3,010,574.80 የውሎ አበል ቅፆችን በአግባቡ ሳይሞሉ ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

2. **ያለሂሳብ አርዕስቱ/መደቡ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፣**

   የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ

በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው መመሪያው ይገልጻል፡፡ በዚሁ መመሪያ መሰረት የገቢና ወጪ ሂሳቦችን መመሪያውን ተከትሎ የሚመዘገብ መሆኑ ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጀስቲክ ዋና መምሪያ በድምር 22,839.60 ያለሂሳብ አርዕስቱ/መደቡ የተመዘገበ መሆኑ፣
- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ ድምር 3,175,574.00 ያለ ሂሳብ አርዕስቱ የተመዘገበ መሆኑ፣
- በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የጤና አገልግሎት ዋና መምሪያ ለተለያዩ አገልግሎቶች የተፈጸመ ክፍያ በድምር 4,851,477.44 ያለ ሂሳብ አርዕስቱ/መደቡ የተመዘገበ መሆኑ፣

በአጠቃላይ ድምር ብር 8,049,891.04 በትክክለኛ የሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው ያለሂሳብ አርዕስቱ/መደቡ የተመዘገበ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>የተሽከርካሪ ጥገና ቅፆችን ሳይሞሉ ለተሽከርካሪ ጥገና የተፈጸመ ወጪ በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል አምስት ልዩልዩ አንቀፅ 13 ሌሎች ድንጋጌዎች እና ቅፆች ተራ ቁጥር 2 የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የሆኑ ቅፆችን መጠቀም እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ኮሚሽኑ ተሽከርካሪዎች ጥገና በሚገቡበትና በሚወጡበት ወቅት በመመሪያ የተቀመጡ ቅጾችን እየተጠቀመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጀስቲክ ዋና መምሪያ በመመሪያው በተዘጋጁ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የጥገና መጠየቂና የጥገና የስራ ትዕዛዝ ቅጾችን ሳይጠቀም ከመመሪያ ውጭ እራሱ ባዘጋጀው በአንድ ወረቀት ላይ በመስራት በድምር ብር 1,789,243.40 ለተሽከርካሪ ጥገና ለተለያዩ ድርጅቶች ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

4. <u>ስራ ላይ ያልዋለ በጀት፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል:: በዚሁ መሰረት ኮሚሽኑ በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው ከ10% በላይ ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፡-

- በፌዴራል ፖሊስ የሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ ከመደበኛ በጀት ብር 746,783,924.39 እና ከካፒታል በጀት ብር 452,178,115.08 በድምር ብር 1,198,962,039.47 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት የተገኘ መሆኑ፣
- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ በድምር ብር 2,581,246.53 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት የተገኘ መሆኑ፣
- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የጤና አገልግሎት ዋና መምሪያ በድምር ብር 875,786.23 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት የተገኘ መሆኑ፣

በአጠቃላይ ድምር ብር 1,202,419,072.23 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት የተገኘ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

<u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)፣</u>

1. <u>የቋሚ እና አላቂ እቃ አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እንዲሁም መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመመሪያው አላማ ግልፅ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር በማስፈን የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት ያዛል። በዚሁ መመሪያ መሰረት ንብረቶች የሚጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ተደረገ፣

* 8

<u>በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ፡-</u>

- መወገድ ያለባቸው የተለያዩ ንብረቶች ሳይወገዱ በንብረት ክፍል ውስጥ የተገኙ መሆኑ፣

<u>~~በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ፡-~~</u>

<u>በለገሀር ያለው የጥገና እቃዎች ግምጃ ቤት</u>

- በለገሀር የሚገኘው የንብረት መጠበቂያ ግምጃ ቤት ለስራ አመቺ ያለሆነ፣ ግቢው በቆሻሻ ፍሳሽ የተሞላ እና ለጤና አስቸጋሪ መሆኑ፣
- ግምጃ ቤቱ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የተሰራ በመሆኑ እና ጣሪያው ስለሚያፈስ ዕቃዎች እየተበላሹ መሆኑ፣
- ግምጃ ቤቱ በውሀ የተሞላ እና ከፍተኛ የሆነ እርጥበት ያለው መሆኑ፣
- የክፍሉ ፅዳት በአግባቡ ያልተጠበቀ በመሆኑ በግምጃ ቤት ውስጥ ያሉ የመንግስት ውስን ሀብት የሆኑ ፌሮ ብረት እና ሚስማር ለዝገት፣ ቺፑድ ለከፍተኛ ብልሽት በተጋለጠ መልኩ ተቀምጠው የሚገኝ መሆኑ፣
- ንብረቶቹ ወይም እቃዎች በአይነት በአይተነት ተለይተው በስርዓት በሽልፍ ላይ ያለተቀመጡ መሆኑ፣
- በግምጃ ቤቱ ውስጥ ያሉ አዲስ እና አሮጌ ንብረቶች ተቀላቅለው የሚገኙ መሆኑ፣
- በእቃ ግምጃ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የሚወገዱ የሊጥ ማቡኪያ ማሽን 50 ኪሎ ብዛት 4፣ አሮጌ ሶፋ፣ የተሰባበረ ሽልፍ፣ ብዛት ያላቸው ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶች፣ ተመላሽ የሆኑ ብረቶች፣ ተቀባሪ ሶኬት ብዛት 481 እንዲሁም የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈ ፒፒሲ ማስቲሽ ብዛት 717፣ ኮስቲክ ሶዳ 15 ኪሎ፣ ነጪ ሲሚንቶ 50 ኪሎ የሚገኙ መሆኑ፣

<u>ቋሚ ንብረት እና የመመገቢያ እቃዎች ግምጃ ቤት</u>

- ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 በአንድ ሰራተኛ የሚሰራ መሆኑ፣
- ግምጃ ቤቱ ፅዳት በአግባቡ ያልተያዘ መሆኑ፣
- የሚሰሩ እና የማይሰሩ ንብረቶች በአንድ ላይ በግምጃ ቤቱ የሚገኙ መሆኑ፣
- የግምጃ ቤቱ መብራት የማይሰራ መሆኑ፣

- መወገድ ያለባቸው በጋዝ የሚሰራ የልብስ ማጠቢያ ማሽን ብዛት አንድ፣ ቤንች ግራይደር ብዛት አንድ፣ ካሽ ሪጂስተር ብዛት ሁለት ሳይወገዱ በግምጃ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣

በአብነት የሚገኘው ግምጃ ቤት

- ከፍተኛ የሆነ የሰቶር ጥበት ያለ በመሆኑ ያሉት የሰራዊት አልባሳት ለመለየት እንዲሁም ለቆጠራ በማይመች መልኩ ተደራርበው እና ተጫጭነው የሚገኙ መሆኑ፣
- በ2014 በጀት አመት አመታዊ የንብረት ቆጠራ ተደርጓል ቢባልም የቆጠራ ሪፖርት ለኦዲት ያልቀረበ እና ቆጠራ ስለመደረጉ በቢን ካርድ ላይ የኮሚቴዎች ፊርማ ያልተደረገ ስለሆነ ቆጠራ አለመደረጉን የሚያመለክት መሆኑ፣

በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የጤና አገልግሎት ዋና መምሪያ፡-

- በወለል 2 እና 3 እንዲሁም በሽንት ቤት ጭምር በረካታ የተለያዩ አይነት በቁጥር 267 መወገድ ያለባቸው መደሃኒቶች አመቺ ባለሆነ መልኩ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

2. **የተሽከርካሪ አያያዝና፤አጠባበቅና አስተዳደር በተመለከተ፣**

በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እንዲሁም የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የመንግስት የተሽከርካሪ ንብረት አስተዳደር በማስፈን የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የተሽከርካሪ ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት ያዛል።

ኮሚሽኑ የተሽከርካሪ አያያዝና፣ አጠባበቅና አስተዳደር በመመሪያ መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጀስቲክ ዋና መምሪያ

- 39 ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተብሎ ጋራዥ የገቡ ቢሆንም ከስድት ወር በላይ በጋራዥ ወስዋ ቁመው የሚገኙ መሆኑን፣
- 6 ከባድ ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው የማይሰራ እና ከስድስት ወር በላይ በጋራጅ ውስዋ ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣
- በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ 74 ከባድ እና 71 ቀላል ተሽከርካሪዎች ያልተወገዱ መሆኑ፣

በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል መከላከል ጠቅላይ መመሪያ፡-

- በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ ብዛት 70 ተሽከርካሪዎች ሳይወገዱ ለረዥም ጊዜ የተቀመጡ መሆኑን፣
- ብዛት 67 ተሽርካሪዎች በጋራዥ ውስዋ ለዋገና ገብተው ለረጅም ጊዜ የቆዩ መሆኑን፣

በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

3. የክትትል ኦዲት በተመለከተ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በየበጀት ዓመቱ የኮሚሽኑ ሂሳብ ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ኮሚሽኑ ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገዋ ኦዲት ሲደረግ፡-

- የ2010 በጀት ዓመት አለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት እና የደመወዝ ክፍያ በድምሩ ብር 31,809.33 ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ያልተመለሰ መሆኑ፣
- የ2011 በጀት ዓመት አለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት፣ የውሎ አበል እና የቤት አበል ክፍያ በድምሩ ብር 1,019,895.84 ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ያልተመለሰ መሆኑ፣
- የ2012 በጀት ዓመት ለሚመለከተው አካል ፌሰስ ያልተደረገ የህክምና መዋጮ፣ ያለአግባብ ለተሽከርካሪ የመድህን ሽፋን የተከፈለ፣አለአግባብ ወደ ግላዊ ሂሳብ የተላለፈው ገንዘብ እና አለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ

በድምሩ ብር 5,888,222.23 ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ያልተመለሰ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ታውቋል።

<u>የህግ ጉዳዮች በተመለከተ(Compliance Issue)፣</u>

1. <u>በውሉ ቀነ ገደብ እቃው ገቢ ባለመሆኑ ያልተቀነሰ የጉዳት ካሳ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16.26 ውል መፈረም ንዑስ አንቀጽ 16.27.4 በንዑስ አንቀጽ 16.27.3 መሰረት (ሸ) አቅራቢው በውሉ በተመከለተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን ማስረከብ (ሀ) አቅራቢው ሳይፈፅም በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1% ወይም 1/1000 የጉዳት ካሳ መክፈል እንዳለበት ይገልፃል፣ ነገር ግን (ለ) የውሉን 10% መበለጥ እንዳሌለበት በግልፅ ተቀምጧል። ከዚህ በተጨማሪም ኮሚሽኑ የፌዴራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ አቅረቢዎች ውል ከገቡበት ቀን ጀምሮ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ዕቃውን ወደ ፌዴራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ መጋዘን ክፍል ገቢ ባለማድረጋቸው አቅረቢዎቹ ላሳለፋቸው ቀናት የውሉን 1/1000ኛ ባዘገዩበት ቀናት ቀንሶ የሚያስቀር መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ፣

- በቀን 14/03/2014 የባንክ የወጪ ማስመስከሪያ 357630 የሂሳብ መደብ 6211 ብር 721,349.00 ከአስቻለው ግርማ ጠቅላላ ንግድ ጋር በ26/01/2014 ባደረገው የውል ስምምነት ለፕሮቶኮል የሚውል ሸሚዝ ለማቅረብ ስምምነቱ ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ 30 ቀናት ውስጥ አጠቃሎ ማስረከብ እንዳለበት በውሉ ቢገልጽም ንብረቱ በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 185239 በ02/03/2014 ገቢ ስለሆነና ስድስት(6) ቀናት ዘግይቶ በማስገባቱ የውሉን ጠቅላላ ዋጋ በቀን 1/1000 ቅጣት (721,349.00*0.001*6) ብር 4,328.09 የጉዳት ካሳ ቅጣት ሳይቀነስ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን፣
- በቀን 30/10/2014 የወጪ ማስመስከሪያ 388092 የሂሳብ መደብ 6216 ብር 6,274,929.00 ከኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ጋር በ05/07/2014 ባደረገዉ የውል ስምምነት ለሰራዊት ግዳጅ ቀለብ የሚሆን

የምንቸት አብሽ ለማቅረብ ስምምነቱ ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ አጠቃሎ ማስረከብ እንዳለበት ቢገለጽም ንብረቱ በደረሰኝ ቁጥር 182725 በ28/10/2014 ገቢ ስለሆነና ሃያ አራት(24) ቀናት ዘግይቶ በመግባቱ የውሉን ጠቅላላ ዋጋ በቀን 1/1000 ቅጣት (6,274,929.00*0.001*24) ብር 150,598.30 የጉዳት ካሳ ቅጣት ሳይቀነስ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 154,926.39 ንብረቱን በውሉ መሰረት በወቅቱ ገቢ ባለማድረጋቸው አቅራቢዎቹ የውሉን 1/1000ኛ ባዘገዩበት ቀናት የጉዳት ካሳ ቅጣት ሳይቆረጥ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል::

2. <u>ከክፍያ መመሪያ ውጪ ንብረቱ ገቢ ከመሆኑ በፊት የተፈጸመ ክፍያ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል አንድ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ዕቃዉ ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረቡን ማረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ኮሚሽኑ በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የጤና አገልግሎት ዋና መምሪያ በቀን 24/10/2014 በክፍያ ማዘዣ ቁጥር 191749 በሂሳብ መደብ 6212 ብር 195,300.0 ለኮምፒዩተር ግዥ ክፍያ የፈጸመ ሲሆን እቃዉ ገቢ የተደረገው በሞዴል ቁጥር 321515 በቀን 29/10/2014 በመሆኑ ወጪው በወጪ ማስመስከሪያ የተፈጸመበት ቀን ዕቃው በሞ/19 ገቢ ከመሆኑ በፊት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>ያለውድድር በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ፣</u>

በፌዴራል መንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 6 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ስራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ ብሎ ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ 2002 መሰረት አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 15/2 እና 15/3 በአዋጁ እና በመመሪያው በተፈቀደው

ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ ተመስርቶ እንደሚከናወን ይገልፃል፡፡ ስለሆነም ግዥዎችን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጀስቲክ ዋና መምሪያ፣

- ለፖሊስ CCTV Camera ኮማንድና ኮንትሮል ግንባታ ስራ ግዥ ከDisiner Touch interior design and finishing ድርጅት ብር 12,255,205.00
- ለሊፍት መለዋወጫ ዕቃ ግዥ ከኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር ብር 2,380,825.98

በድምር ብር 14,636,030.98 በግልፅ ጨረታ መፈጸም ሲገባው ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የተፈፀመ ከመሆኑ በተጨማሪ በስራ ተቋራጩ እና በኮሚሽኑ መካከል የተደረገ የስራ ስምምነት የውል ሰጪ ክብ ማህተም በእያንዳንዱ የስምምነት ገፅ ላይ የሌለ መሆኑ እና ከክፍያ ሰነዱ ጋር የተየያዘው ውል ከማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ ቀድሞ የተሰራ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>በግልጽ ጨረታ መገዛት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተገዛ ግዥ፣</u>

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዢ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ እንዲሁም ሰኔ 2002 የወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 በአዋጅና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው ያዛል፡፡ በተጨማሪም የገንዘብ ሚንስቴር በቀን 25/01/2014 ባወጣው የግዥ ማሻሻያ መመሪያ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ መገዛት ያለበት ለዕቃዎች እስከ ብር 400,000 እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ስለሆነም በመመሪያው መሰረት ግዥን ያከናወነ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጀስቲክ ዋና መምሪያ በቀን 16/10/2014 የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 267154 በሂሳብ መደብ 6252 ብር 3,942,040.0 የመድረክ ማስዋቢያ ዲኮሮችና የሁነት ዝግጅት የኪራይ አገልግሎት ግዥ በግልጽ ጨረታ መግዛት ሲገባዉ ከዲሲቲ ኢንተርቴይመንት ከመመሪያ ውጭ በዋጋ ማወዳደርያ ግዥ ተፈፅሞ የተገኘ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

5. <u>በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ "ለ" የስራ ማስኬጃ ቅድመ ክፍያ በ 7 ቀናት መወራረድ እንዳለበትና በንዑስ አንቀጽ "መ" ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ ስለሆነም በመመሪያው መሰረት እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሰኔ 30/2014 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት ላይ ከተገለፀው የተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ፡-

- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ በድምሩ ብር 956,305,292.11 በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታይ መሆኑን፣
- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ በድምሩ ብር 7,808,072.69 ከአንድ ወር እስከ አስር ዓመት በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ የሚታይ መሆኑን፣
- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የጤና አገልግሎት ዋና መምሪያ በሂሳብ መደብ 4253(ለግለሰቦች እና ለድርጅቶች ለእቃ አቅራቢዎች) በድምሩ ብር 51,591,951.68 ቅድመ ክፍያ በደንቡና በመመሪያው መሰረት ማወራረድ ሲገባው እስከ አምስት ዓመት ድረስ ሳይወራረድ የተገኘ መሆኑን፣

በአጠቃላይ ድምር ብር 1,015,705,316.48 በወቅቱ መወራረድ ሲገባው ያልተወራረደ ውዝፍ የተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

6. <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ፣</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 በተራ ቁጥር 5 የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ፣ በንዑስ አንቀጽ ‹‹ ሀ›› ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲቀርብና

ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንዳለበት እና በንዑስ አንቀጽ ‹‹ሐ›› መ/ቤቶች ከተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብርና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለባቸው መመሪያው ያዛል፡፡ ስለሆነም በመመሪያው መሰረት እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሰኔ 30/2014 በጀት ዓመት በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ከተገለፀው ውስጥ፡-

- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጂስቲክስ ዋና መምሪያ በድምሩ ብር 32,159,933.02 በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ መከፈል ሲገባው ውዝፍ የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታይ መሆኑ፣
- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ በድምሩ ብር 2,545,735.63 በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ መከፈል ሲገባው ውዝፍ የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታይ መሆኑ፣
- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የጤና አገልግሎት ዋና መምሪያ በሰኔ 30/2014 በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ከተገለፀው ውስጥ በሂሳብ መደብ 5054 በድምሩ ብር 583,814.84 በደንቡ እና መመሪያው መሠረት ለባለ መብቱ ሳይከፈል በተከፋይ በሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታይ መሆኑ፣

በአጠቃላይ ድምር ብር 35,289,483.49 ውዝፍ የተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ መወራረድ ሲገባው ያልተወራረደ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

7. <u>ከተፈቀደው በጀት በላይ የተጠቀሙ መሆኑን፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል:: በተጨማሪም በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት ኮሚሽኑ በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው ከ10% በላይ ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፡-

በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ ከመደበኛ በጀት ብር 49,711,136.69 ለየሂሳብ መደቦች ከተደለደለው የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ ከበጀት በላይ የተጠቀመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት